# ክብር ቅዱስ መስቀል

ቅዱስ መስቀል ስንል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ከሞተ ኃጢአት ለማዳን በቀራንዮ የተሰቀለበተ የተመሳቀለ ዕፅ ማለታችን ነው። ሊቃነ ካህናትና መስፍኑ ጲላጦስ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በመስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት በፈረዱበት ጊዜ ወታደሮቻቸው ጌታችንን መስቀሉን አሸክመው ወደ ቀራንዮ ወሰዱት፣ «ወወሰድዎ ጨነዘ ይጸውረ መስሉ» መሰቀሉን እንደ ተሸከመ (ተሸክሞ) ወደ ቀራንዮ ወሰዱት እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ (ዮሐ. ፲፱፥፲፯)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲጓዝ፣ እየጣደፉና እየገፉ ሲወስዱት እጅግ ደከመ፤ በዚህ ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም ጫኑበት (ሉቃ. ፳፫፥፳፮)። ከዚህም እንደ ገና ራሱ ጌታችን መስቀሉን ተሸክሞ ቀራንዮ ደረሰ፤ ከዚያም እንደ ደረሰ በመስቀል ሰቀሉት፤ በቀኙና በግራውም በኩል ሁለት ወንበዴዎችን ሰቀሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ መከራ መስቀልን በመቀበል በዕለተ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት በፈቃዱ ስለ እኛ ሞተ፤ በአሥራ አንድ ሰዓት ገደማም ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አወርደው በአዲስ መቃብር ቀበሩት (ሉቃ. ፳፫፥፶-፶፮፤ ዮሐ. ፲፱፥፴፰-፵፪)።

## ክርስቶስ በመስቀሉ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ቅዱስ ደሙ ሰላምን አወጀ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ታላቅ ምስጢር ሲናገር፣ «በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ በሰማያትም በምድርም ላሉት እርቅን፣ ሰላምን አደረገላቸው» ብሎአል (ቈላ. ፩፥፲፱)።

ጌታችን በመስቀሉ ጠላት ዲያብሎስን እንደ ገደለ ማለት እንዳሸነፈና ተለያይተው የነበሩትንም ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ማድረጉን አስመልክቶ በሌላው መልእክቱ ሲናገር፣ «አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናቹህ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል፣ እርሱ ክርስቶስ ሰላማችን ነው፤ እርሱ ሁለቱን ያዋሐደ፣ የትእዛዙንም ሕግ (ሕዝብንና አሕዘብ የመባልን ትእዛዝ) ሽሮ በመካከል የነበረውንም የጥል ግድግዳ በሥጋው አፈረሰ፤ ይኸውም ከሁለታችሁ አንድ አዲስ ሰውን ይፈጥር ዘንድና ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፣ ጥልን በመስቀሉ ገደለ፤ በእርሱም ሁለታችሁን በአንደ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፤ መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁትና ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን ሰጣቸው» ማለት ነው(ኤፌ. ፪፥፲፫-፲፮)።

ከዘሁ በላይ እንደ ተመለከትነው ጌታችን ስለ ዓለሙ ቤዛ የተሠዋበት ቅዱስ መስቀል ክበር ነው፤ ጠላት ዲያብሎስን ያሸነፈበት ቅዱስ መስቀል ክቡር ነው፤ በደሙ በከበረው ቅዱስ መስቀል ለምድራውያንና ለሰማያውያን ሰላምን አውጀአል። ሐዋርያው እንዳለው፣ ቅዱስ መስቀል የሰላምና የደኅንነት ንጉሥ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋን ነው። በእግዚአብሔር አብ ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ (በሞት አንሶ) የነበረውን ከሞት የተነሣ የምስጋናን ዘውድ (አክሊለ ስብሐት) ጭኖ (ደፍቶ) እንሆ አናየዋለን» (ዕብ. ፪፥፱-፲)።

ስለዚህ ቅዱስ መስቀል ንጉሠ ስብሐት ክርስቶስ (የምስጋና ንጉሥ ክርስቶስ) የተሠዋበት፣ ክርስቶስ አምላካችን በቅዱስ ደሙ ያከበረውና መለከታዊ ደሙም የፈሰሰበት ስለ ሆነ በአማን (በእውነት) ክበር፣ በእውነት ቅዱስ ነው። በመሆኑም በእውነት ክርስቶሳውያን የሆን ሁሉ በጌታችንና በክቡር መስቀሉ እንመካለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያስተምር «እኔስ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ» ብሎአል (ገላ. ፮፥፲፬)።

በዚሁ መሠረት የክርስቶስ ተከታይ ነኝ የሚል ሁሉ ክርስቶስን ከልብ ማመንና መውደድ፣ መስቀሉንም ማክበር ይገባዋል። እንደ ሐዋርያው እንደ ቅዱስ ጳውሎስም በክርስቶስ መስቀል መመካት ግዴታ ነው።

# መስቀል መሳለም (መሳም)

እኛ ክርስቶሳውያን የክርስቶስን መስቀል የምንስመው ወይም የምንሳለመው ስለ ክርስቶስ ያለንን ፍ ቅር ለመግለጽና በረከተ ክርስቶስንም ለመቀበል ነው።

ለምሳሌ፡-

፩ኛ. ከሩቅ አገር ከወንድማችን ወይም ከጓደኛችን የተላከልንን ሥዕል ገጽ ማለት ፎቶግራፍ ስመን እንቀበላለን፤ ይኸውም ናፍቆታችንና ፍቅራችንን ለመግለጽ ነው።በዚህ መሠረት የክርስትና ሕይወታ ችን መለያ ምልክት የሆነውን መስቀል ስናይ ጌታችንን ከመውደዳችን የተነሳ እንስመዋለን (እንስማ ዋለን)።

፪ኛ. ጀግኖችና ዐርበኞች ወታደራዊ አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ቃለ መሓላ ሲፈጽሙ የአገራቸ ውን ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) ተንበረክከው ይሳለማሉ፤ ማለት ይስማሉ፣ ይኸውም ለአገራቸው ፍቅ ራቸውንና ታማኝነታቸውን ለመግለጽ ነው። በዚህም መሠረት እኛም የመንግሥተ እግዚአብሔር ም ልክት (ባንዲራ) የሆነውን ቅዱስ መስቀልን የምንሳለመው ወይም የምንስመው ስለ ጌታችን ያለንን እምነትና ፍቅር ለመግለጽ ነው፤ ቀጥሎም ረድኤትንና በረከትን ለመቀበል ነው።

፫ኛ. አንደ ሰው ከተወለደበት አገር ርቆ በስደት ወይም በትምህርት ምክንያት፤ ወይም በሥራ ምክ ንያት በርከት ላሉ ዓመታት በባእድ አገር ተቀምጦ ወደ አገሩ ሲመለስ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገሩን መ ሬት ሲረግጥ ተንበርክኮ መሬትዋን ይስማል፤ የኸውም አክበሮቱንና ናፍቆቱን ለመግለጽ መሆኑ ግል ጽ ነው። በዚህ ኣይነት አምላካዊ ደም የፈሰሰበትን ቅዱስ መስቀልን የምንስመው ስለ ጌታችን ያለ ንን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽና ከቅዱስ መስቀሉም  በረከት ለመቀበል ነው። ነገር ግን የክርስቶ ስን መስቀል መሳማችንን ወይም መሳለማችንን የሚነቅፉ እንደ ሞኝነትም አድርገው የሚያስቡ ወይ ም የሚቆጥሩ ወገኖች አሉ። በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን አፅራረ መስቀል አስመ ልክቶ ለእውነተኞቹ ክርስቲያኖች እንዲህ ሲልጽፎአል... «የመስቀሉ ቃል (ነገር) ለሚጠፉት ሞኝነት ፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው...» ብሎአል (፩ ቆሮ. ፩፥፲፰)።

በሌላ መልእክቱም... «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው የመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እን ሱ ነግሬያችኋለው፤ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ፤ እነሱ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ አሳባቸው ምድራዊ ነው...» ሲል አስተምሮአል ( ፊልጵ. ፫፥፲፱)።

መስቀል መሳለምና ማክበር በእርግጥ ፍቅርን ለመግለጽ፤ በረከትም ለመቀበል ነው። መሳለም ወይም መሳም የአክብሮት፣ የፍቅርና የናፍቆት መግለጫ መሆኑም በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ታሪኳ በቅዱስ ወንጌል ተመዝግቦላት የሚገኝ አንዲት ኃጢአተኛ ሴት እጅግ ብዙ የሆነውን ኃጢአ ትዋን ጌታ እንዲተውላት እጅግ አድርጋ ጓጓች። ጌታችንንም አጥብቃ ፈለገች። ባገኘችው ጊዜ ሽ ቱ የሞላበት የአልባጥሮስ ብልቃጥ(ጠርሙስ)አመጣች. ከጌታም በስተኋላው  በእግሩ አጠገብ ቆማ እየአለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርሰው (ታጥበው) ጀመረች. በራስ ጠጉሩአም ታብሰው፣እግሩንም ት ስመው (ታጥብ)ጀመረች፤ እንደዚህም በማድረጓ ጌታችን ኃጢአትዋን ይቅር ብሎ ልጄ በሰላም ሂ ጂ ብሎ አሰናበታት (ሉቃስ.፯፥፴፮-፶)።

በዚሁ ዓይነት ጌታችንን የሚወድና ትእዛዙን የሚጠብቅ ክርስቲያን ሁሉ ስለ ጌታ ያለውን መንፈሳዊ ፍቅር ለመግለስ፣ እንዲሁም ሥርየተ ኃጠአትንና በረከትን ለመቀበል የጌታ እግሮች የቆሙበትን ቅ ዱስ መስቀል ይስማል (ይሳለማል። የጌታ አግሮች ከቆሙበት ቦታ መስገድ እንደሚገባ ቅዱስ መጽ ሐፍ ያረጋግጣል። «የጌታ እግር በቆመበት ስፍራ እንሰግዳለን»ሲል ንጉሥ ዳዊት መስክሮአልና፣ ( መዝ. ፩፻፴፩፤(፩፻፴፪)፤፯)።

የተቀደሰውን ነገር ወይም ቦታ መሳለም ደግሞ በሃይማኖት ሥርዓት የተለመደ ነው። በቤተ መቅደስ ወይም በምኩራብ ለጸሎት ይሰበሰቡ የነበሩ እስራኤላውያን መጽሐፈ ሕግ ማለት ኦሪት (ቶራ) ከተን

በበ በኋላ ለጸሎት የሚሰበሰቡትን ሰዎች በሙሉ መጽሐፈ ኦሪቱን ይሳለሙ ወይም ይስሙ እንደነበር መጽሐፈ ታልሙድ ይመሰክራል። ይህን ሥርዓት አሁንም በምኵራባቸው እየሠሩበት ነው።እኛም እንደ ጥንቱ ሥርዓት ቅዱስ ወንጌልን፣ መስቀልንና ሥዕልን እንሰማለን (እንሳለማለን)። በቅርብም ሆነ በሩቅ ያለውን

ቅዱስ ቦታ ወይም ቅዱስ መስቀል መሳም (መሳለም) ስለሱ ያለንን አክብሮትና ፍቅር ለመግለጽ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዻውሎስም ስለዚሁ ሲገልጽ «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፤ የተሰጣቸው የተስፋ ቃል አላገኙም፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት» ይላል (እብ.፲፩፤፲፫)። የወደዱትንና ያፈቀሩትን ነገር እንኳንስ በቅርብ ተገኝተው መሳለም (መሳም) ይቅርና በሩቅ ሆነው እንኳን መሳለም እጅ መንሳት እንደሚገባ ሐዋርያው የጻፈው ቃል ታላቅ ምስክር ነው።

ከዚሁ መጽሐፈ ቅዱሳዊ ሥርዓት የተነሳ በሀገራችን በኢትዮጵያ በተለይም በገጠሩ ክፍል በየመንገዱ መሳለሚያ እየተባለ የሚጠራ ልዩ ቦታ ይገኛል። በዚሁ ቦታ መስቀል መሰል የድንጋይ ካብ ይገኛል። ሕዝበ ክርስቲያኑ በመንገዱ ሲያልፍ ከዚያቦታ እንደደረሰ ቀጥ ብሎ የቆምና በተተከለው የዕንጨት መስቀል ወይም በተቆለለው መስቀል መሰል ካብ አቅጣጫ ወደሚገኘው ቤተክርስቲያን ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ ይነሳል፣ማለትም ይሳለማል። ወይም የመሳለሚያውን አቅጣጫ ተከትሎ በሩቅ ለሚየው ቤተክርስቲያን ይሰግዳል። ይኸውም እምነቱንና ፍቅሩን ለመግለጽ ነው።

ነቢዩ ዳንኤል የጸሎት ቤቱን መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ አድርጎ በመሥራት፣ በቀን ሦስት ጊዜ መስኮቶችን እየከፈተ በቀን ሦስት ጊዜ ተንበርክኮ ይጸልይ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዳን. ፮፤፲)። ስለዚህ መስቀል መሳለም ወይም ወደ መስቀልና ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ እንደዚሁም ወደ ቅዱሳን ሥዕሎች ዞሮ መስገድ የሚገባ መሆኑን አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች።

## <u>በመስቀል መባረክ</u>

ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት በቅዱስ መስቀል እንዲባርኩና ምእመናንም እንዲባርኩ ኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስትያን ታዛለች።

### በቅዱስ መስቀል የመባረክና የመባረክ ምስጢር

፩ኛ. በጌታችን ቅዱስ መስቀል አማካይነት ሥርዓት ኃጢአትን ለመቀበል፣
፪ኛ. በጌታችን ቅዱስ መስቀል አማካይነት ቡራኬን ማለት መንፈሳዊ ክብርንና
ጸጋን ለመቀበል ነው።

በመስቀል ምሳሌ በረከትንና ምርቃትን መስጠት በዘመነ ኦሪትም የተለመደ ነው። በእርግጥ በኦሪት ዘመን መስቀል አልነበረም። ስለዚህ አበው በመስቀል ምሳሌ እጃቸውን እየዘረጉ ልጆቻቸውን ይባርኩ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ለምሳሌ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እንመልከት። ያዕቆብ በሸመገለ ጊዜ የልጅ ልጆቹን ኤፍሬምንና ምናሴን ሊባርካቸው ፈለገ፤ አባታቸው ዮሴፍም ሁለቱን ልጆቹን በያዕቆብ ቀኝና ግራ አቆማቸው፤ ያዕቆብም እጆቹን አመሳቅሎ ባረካቸው፤ መረቃቸውም (ዘፍጥ.፵፰፤ ፰–፳፪)።

በዚሁ ዓይነት ካህናተ ኦሪት እጆቻቸውን በማንሣትና በማመሳቀል ሕዝቡን ይባርኩ ነበር። የቡራኬም ሥርዓት ከእግዚአብሔር የተነገረ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነግሮት ነበር፤«ለአሮንና ለልጆቹ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ የእስራኤልን ልጆች ስትባርኳቸው እንዲህ በሉአቸው፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ይመልስ፤ እግዚአብሔር ሰላምን ይስጥህ። በዚሁ ዓይነት ስሜን በእስራኤል ልጆች ላይ ያደርጋሉ፤ እኔም እባርካቸዋለሁ» (ዘኁል. ፮፤ ፳፪-፳፯)።

## <u>የበረከት ባለቤት ጌታችን</u>

የበረከት ባለቤትና የበረከት መገኛ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወንጌል በሚያስተምርበት ጊዜ የተቀደሱ እጆቹን እያነሣ (እያመሳቀለ) ምእመናንን ይባርክ ነበር። ለምሳሌ ጌታችን በስብከተ ወንጌል ጊዜ ለመባረክ ወደ እሱ የመጡትን ሕጻናት ተቀብሎ እንዳቀፋቸውና እጆቹቹንም አንሥቶ (አመሳቅሎ) እንደባረካቸው ቅዱስ ወንጌል ይመሰክራል(ማር. ፲.፤፲-፲፫)። ከሙታን ተለይቶን ከተነሣም

በኋላ ወደ ሰማያት ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ እጆቹን አንስቶ (አመሳቅሎ) ባረካቸው ፤ እንደባረካቸውም ወደ ሰማያት ማረጉን ሉቃስ መስክሮልናል (ሉቃ. ፳፬፤፶)።

ስለዚህ ጌታችን በሠራው ሥርዓት መሠረት የጌታችን ተከታዮች የሆኑት ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶ ሳትና ካህናት(ቀሳውስት) በቅዱስ መስቀልና እጆቻቸውንም በማሳቀል ምእመንንና ምእመናትን እንዲ ባርኩ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ታስተምራለች።

## <u>ማማተብ</u>

<u>«አማዕተበ» አመሳቀለ፣ አማተበ፣ ባረከ</u> ካለው ግሥ የወጣ ቃል ነው። ትርጉሙ ምልክት ማድረግ፤ ማመሳቀል መባረክ ማለት ነው። ማዕተብ ማለትም ምልክት ማለት ነው። «ማዕተበ ክርስትና» ሲል የክርስትና ምልክት (መስቀል) ማለት ነው። ባረከ ሲልም «ዮሴፍ አባቱ እሥራኤል ይባርካቸው ዘን ድ ልጆቹን አቀረበ። እሥራኤልም እጆቹን በራሳቸው ላይ አመሳቀለ» ይላል (ዘፍጥ. ፵፰፤ ፲–፳፪)።

ስለዚህ በቀኝ እጅ በጣቶች በመስቀል ምሳሌ (በአርአያ መስቀል) ማማተብ ተገቢ መሆኑን ኦርቶዶክ ስ ቤተ ክርስትያን ታዛለች። ፍትሕ መንፈሳዊ (ፍትሐ ነገሥት) በተባለው የቀኖና (የሕግ) መጽሐፍ በ አንቀጽ ፲ በቁጥር ፭፻፴፪ ላይ ማማተብ የሚገባ መሆኑን ተደንግጓል። ትእዛዙም ቀጥሎ ያለው ነው ።

«በመስቀል አምሳል (በመስቀል መሳሌ) ከላይ ወደታች (ከግንባራችን ወደ ደረታችን)፣ከግራ ወደ ቀኝ በጣት ማማተብ ነው። በጣቶች የማማተብ አጋንንትን (ሰይጣናትን)ለማራቅ ነው። ጌታችን «እኔ በእግ ዚአብሔር ጣት አጋንንትን (ሰይጣናትን) አስወጣሁ ብሎ እንደተናገረ (ሉቃ.፲፩፤፳)።

ከላይ ከግንባራችን እስከ ታች ማለት እስከ ደረታችን ማማተባችን ግን ጌታችን መድኃኒታችን ከሰማ የ ሰማያት መውረዱን፣ መሰቀሉን መሞቱንና ከሙታን ተለይቶ በመነሣት እኛን ከግራ ወደ ቀኝ የመ መለሱ ምልክት ነው። በመስቀል አምሳል ማማተብ ድኅነታችን የተፈጸመው በመስቀል ነውና፣ ሰይ ጣን ከእኛ የጨርቅ ዘንድ በተረዳች ሃይማኖት (ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት) ዘወትር በመስቀል አምሳል ፊታችንን እናማትባ ዘንድ ከጥፋትም እንድንበት ዘንድ ይህንን ምልክት (ማማተብ ) ሐዋርያት ለእኛ አደረጉ፤ ይኸውም የግብጻውያንን በኵር እንደ ገደለ፣ በኵራቸውን እንዳይገድልባቸው እግዚአብሔ ር በፋሲካ የሚታረደውን የበግ ደም ከእስራኤላውያን ልጆች ቤት የሚያርቅ ምልክት እንዳደረገው ነ ው። በትምህርት መስቀል ማለት ምልክት የምናማትብባቸው ጊዜያቶችም:

አንደኛ - ጸሎት ስንጀምር
ሁለተኛ - ነገረ መስቀልን የሚያነሳ ቃል ስናነብ ነው።
(ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፬ ቁጥር ፭፻፴፪–፴፫)።

እንደሚታወቀው ወደ ቤተ ክርስቲያን ደርሰን ስግደት ስናደርግ እጃችን በዘፈቀደ ሥርዓትና ምስጢር በሌለው ሁናቴ ማወዛወዘዝ ሳይሆን፣ በመኸከለኛው ጣታችንና ባመልካቹ ጣታችን የመስቀል ቅርጽ በ መሥራት ከግንባራችን ወደ ደረታችን፣ ከዚያም ከግራ ትከሻችን «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅ ዱስ» እያልን ማማተብ ተገቢ ነው። ይኸውም ከላይ እንደተገለጸው ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎና ሞ ቶ በትንሳኤው አዳምንና የልጅ ልጆቹን ከግራ(ከዲያቢሎስ) ወደ ቀኝ ማለት ገነት የመመለሱ ምሳሌ ነው።

ወይም በምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስትያናት እንደሚሠራበት ሁለቱን ጣቶቻችንን ከአውራ ጣቶ ቻችን በማገናኘት፣ «በስመ አብ» ስንል ግባራችንን እንነካለን፤ «ወወልድ ስንል ልባችን (ደረታችንን) እንነካለን፤ «ወመንፈስ ቅዱስ» ስንል ትከሻችንን እንነካለን፣ አሐዱ አምላክ ስንል ግራ ትከሻችንን በመንካት እንጨርሳለን። ይኸውም በመስቀል ምሳሌ በአብ፣ ወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ በ አንድ አም ላክ ስም ሰይጣናትን (አጋንንትን) ማራቃችን ነው። (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፬ ቁጥር ፭፻፴፫)።

የማማተብ ጊዜያትም ከላይ ከተገለጸው ሌላ በተጨማሪ ጸሎት ስንጨርስ እግዚኦ ተሣሃለነ (ኪርያላ ይሶን) ስንል ከምግብ በፊት ምግብ ተመግበን ስንፈጽም፤ ስንተኛ፤ ከመኝታችንም ስንነሳ፤ ከቤታችን ስ

ንወጣን ወደ ቤታችን ስንገባ፤ ሥራ ስንጀምርና ስንጨርስ፤ ክፉና አስደንጋጭ ነገር ስንሰማ ወይም ስ ናይ ከጸሎት ጋር ማማተብ ይገባናል።

<u>አስተውል</u> ይህ የዚህች መጽሐፍ ደራሲ አስተያየት ነው።

ቀደም ብለን እንደገለጽነው በትምእምርተ መስቀል (በመስቀል ምሳሌ) ማማተብ ክፉን ለማራቅና መን ፈሳዊ ኃይልን ለማግኘት ነው። ምክንያቱም የክርስቶስ ቅዱስ መስቀል መንፈሳዊ አጥራችን፤ ኃይላች ንና ጽናታችን ነውና።

መስቀል ኃይልና ጽንእ በመሆኑ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በመስቀል ምሳሌ ነው። ማ ለት የሰው ቅርጽ የመስቀል ቅርጽ ነው። አእዋፍና አሞሮችም የተፈጠሩት በመስቀል ቅርጽ ነው። መስቀል ኃይልና ጽንእ በመሆኑ ትምርተ መስቀል (የመስቀል ምሳሌ) በብዙ ፍጥረታት ዘንድ ይገኛል። ይህንንም አስመልክቶ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድሪያ የጻፈው እንመልከት። «ትምእርተ መስቀል ( የመስቀል ምሳሌ) በሁሉም ፍጥረቶች ዘንድ ትገኛለች፤ ፀሐይ በመስቀል አምሳል ብርሀንዋን ካልዘረጋ ች ልታበራ አትችልም። ጨረቃም እንደዚሁ። የሰማይ ወፎችም (ማንኛውም ወፍ) ክንፋን በመስቀል አምሳያ ከልዘረጋች ለመብረር አትችልም ሲል ቅዱስ አትናቴዎስ አረጋግጦአል (መጽ. ግብረ ሕማማ ት ዘዓርብ ገጽ(፫፻፴፩–፫፻፴፪)።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ መስቀል ክቡርና አጋንትንም የሚያርቅ መሆኑን፣ ለሱም የአክብሮት ስግደት እንደሚገባው መስክሮአል እንዲህ ሲል፤ «ለመስቀል ስግደት (የክብር ስግደት) ይገባል፤ ይህ መስቀል ነገሥታት መኳንንት መሳፍንት የሚያከብሩት ብፁዕና ምስጉን ነው፤ ይህ መስቀል ለሰው ል ጅ ሁሉ ማጽኛ (ማጠንከሪያ) ነው። በርሱም አጋንንት ሁሉ ይሸሻሉ፤ ርጉም ሰይጣንም ይደነግጣል፤ እሱን መላእክት ያከብሩታል፤ ሰማዕታትም ያመሰግኑታል፤ ሐዋርያትም ዝናውን ይናገሩበታል፤ መድኃ ኔዓለም በሱ ተሰቅሎአልና፣ ቤተ ክርስትያን ትሸልመዋለች» ማለት ነው።( ግብረ ሕማማት ገጽ ፴)።

በሌላ ክፍልም ይህ ቅዱስ አባት ስለ ቅዱስ መስቀል ክብርና በመስቀል አምሳል ስለማማተብ እንዲህ ሲል አስተምሮአል። «ወንድሞች ሆይ ከአሁን ጀምሮ ሁል ጊዜ የጌታችን የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ማሰብ አናቋርጥም (አናስታጉልም)፣ መስቀል የመልካም ነገር ሁሉ ራስ፣ የሕይወ ትና የመድኃኒት መጀመሪያ፣ የድል አክሊል ነውና፣ ምክንያቱም መስቀል ከክፉ ሰይጣን ጥቃት የም ንድንበት ምልክታችን መዳኛችን ነውና። ስለዚህም በመስቀል ፊታችንን ማማተብ፣ የመስቀል መስል በዕቃዎቻችን በሰብላችን ማድረግ ይገባናል፣ ልባችንም በመስቀል በማማተብ ከጠላት (ከሰይጣን) እን ጠብቃለን፣» ሲል አስተምሮአል፣ (ግብረ ሕማማት ዘዐርብ ገጽ ፫፻፶፩–፫፻፶፪)።

ስለዚህ እውነተኛ ክርስትያን የሆኑ ሁሉ ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ቅዱስ መስቀልን ማክበር ን መሳለም (መሳም) ይገባዋል። ነገር ግን መስቀልን አላከብርም፣አልስምም፣ አልሳለምም የሚል ወገ ን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፣ የመስቀል ጠላት መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስን የሚወድ ሁሉ መስቀሉን መውደድ፣ ማክበርና መሳለም ይገባዋል።

ቅዱስ መስቀል ኃይላችን ነው
ቅዱስ መስቀል ጽንዓችን ነው
ቅዱስ መስቀል መመኪያችን ነው
ቅዱስ መስቀል ቤዛችን ነው

ቅዱስ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው። (ከዘወትር ጸሎት የተጠቀሰ)

**አቡነ ገብርኤል «ክብረ ቅዱሳን» በሚል ርዕስ በ1990 ዓ.ም ካሳተሙት የተቀዳ።**